'አንድ ሰውዬ ውዱእ አደረገና እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል ስፍራ ተወ። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተመለከቱትና እንዲህ አሉት: ‹ተመለስና ዉዱእህን አሳምር!› ተመልሶ (አስተካከለና) ከዚያም ሰገደ።'

ከጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው: እንዲህ አለ: "ዑመር ቢን አልኸጧብ እንዲህ ብሎ ነገረኝ: 'አንድ ሰውዬ ውዱእ አደረገና እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል ስፍራ ተወ። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈንና) ተመለከቱትና እንዲህ አሉት: ‹ተመለስና ዉዱእህን አሳምር!› ተመልሶ (አስተካከለና) ከዚያም ሰገደ።'"
[በማመሳከሪያዎቹ ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ዉዱእ አድርጎ የጨረሰን ሰውዬ እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል የዉዱእ ውሃ ያልነካት ስፍራን እንደተመለከቱበት ተናገሩ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ተወው ስፍራ እየጠቆሙ እንዲህ አሉት: ተመለስና ዉዱእህን አሳምር! አሟልተህ አድርግ! ለሁሉም አካልህ ከውዱኡ ውሃ የሚገባውን ሐቅ ስጠው አሉት! ሰውዬውም ተመለሰና ዉዱኡን አሟልቶ ሰገደ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/8386